የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፪ኛ ዓመት ቁጥር ፴፯
አዲስ አበባ ሐምሌ ፫ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32th Year No. 37
ADDIS ABABA, 10th July, 2026

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፳፩/፪ሺ፲፰

በኢትዮጵያ መንግስት እና በሩሲያ ፌዴሬሽን መካከል የጋራ የባዮሎጂ ምርምር ማዕከል ለማቋቋም የተፈረመውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ…………...............…................…ገጽ ፲፱ሺ፯፻፸፱

## Content

Proclamation No. 1421/2026

Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Russian Federation on the establishment of the Joint Ethiopian-Russian Biological Research Center Ratification Proclamation......
…...........................................…....Page 19779

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፳፩/፪ሺ፲፰

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሩሲያ ፌዴሬሽን መካከል የጋራ የባዮሎጂ ምርምር ማዕከል ለማቋቋም የተፈረመውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሩሲያ ፌዴሬሽን መንግስት መካከል የተደረገው የጋራ የባዮሎጂ ምርምር ማዕከል ማቋቋሚያ ስምምነት እ.ኤ.አ ጁላይ ፳፯ ቀን ፪ሺ፳፫ በሴንት ፒተርስበርግ የተፈረመ በመሆኑ፤

### PROCLAMATION No. 1421/2026

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE RUSSIAN FEDERATION ON THE ESTABLISHMENT OF THE JOINT ETHIOPIAN-RUSSIAN BIOLOGICAL RESEARCH CENTER

**WHEREAS**, the Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Russian Federation on the establishment of the Joint Ethiopian-Russian Biological Research Center was signed at Saint Petersburg on the 27th day of July, 2023;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

ስምምነቱ በስራ ላይ የሚውለው በሁለቱ ተዋዋይ አገሮች ሕጎች መሠረት ስምምነቱ መጽደቁን ከሚያረጋግጡ ሠነዶች ልውውጥ በኋላ እንደሚሆን በስምምነቱ ውስጥ በመመልከቱ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም ባካሄደው ፳፫ኛ መደበኛ ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ ቁጥር (፩) እና (፲፪) መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ መንግስት እና በሩሲያ ፌዴሬሽን መካከል የጋራ የባዮሎጂ ምርምር ማዕከል ለማቋቋም የተፈረመውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፳፩/፪ሺ፲፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. <u>ስምምነቱ ስለመጽደቁ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሩሲያ ፌዴሬሽን መንግስት መካከል ሐምሌ ፳ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም የጋራ የባዮሎጂ ምርምር ማዕከል ለማቋቋም የተፈረመው ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**WHEREAS**, it is stipulated in the Agreement that the Agreement shall come in to force after the exchange of notes confirming its ratification incompliance with the respective legal procedures in force in each country;

**WHEREAS**, the House of Peoples Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified this agreement at its 23rd Regular Session held on 4th day of June, 2026;

**NOW THEREFORE**, in accordance with Article 55 Sub Articles (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Russian Federation on the establishment of the Joint Ethiopian-Russian Biological Research Center Ratification Proclamation No. 1421/2026''.

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Russian Federation on the establishment of the Joint Ethiopian-Russian Biological Research Center signed at Saint Petersburg on 27th day of July, 2023 is here by ratified.

፫. <u>የሥምምነቱ አስፈጻሚ አካል</u>

ይህን ሰነድ ከሌሎች የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር እንዲያስፈጽም የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በዚህ አዋጅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፫ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም**

**ታዬ አጽቀሥላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

3. <u>**Implementing Organ**</u>

The Ministry of Science and Technology of the Federal Democratic Republic of Ethiopia in collaboration with the relevant government organs is hereby is designated to implement this Agreement.

4. <u>**Effective Date**</u>

This Proclamation shall come into force up on publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 10th day of July, 2026**

**TAYE ATSKESELASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDRAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**